

# 2ኛ እድሎች፡የ ቲኦ ኔዝ ትንሳኤ



ታዲያስ ውድ ወንድሞችና እህቶች። ስሜ ቲኦ ኔዝ ይባላል እናም የምኖረው ፋርሚንግተን ኒው ሜክሲኮ ውስጥ ነው። ዛሬ የእኔን ምስክርነት ላጋራችሁ እወዳለሁ፥ እግዚአብሔር ለእኔና ለቤተሰቤ አስገራሚ ተዓምራዊ ነገር እንዳደረገልን። ውድ የሆነውን ማዳኑን ወደ ቤታችን አመጣ።

በ1995 (እ.ኤ.አ.) አመጸኛ ሰው ነበርሁ። እጠጣና እጾችን እጠቀም ነበር፥ ስለምንም አልጨነቅም ነበር። አንድ ቀን በፍጥነት ከመጠን በላይ ጠጣሁና ልቤ ቆመ። ለአራት ሠዓታት ያህል ሞትሁ።

አሁን የምነግራችሁ ነገር ስለሞትና ስለሕይወት ሁለቴ እንድታስቡ ያደርጋችኋል። ልቤ መምታት ስታቆም፥ የምድር ጫጫታ ሁሉ ደብዝዞ ጠፋና ሙሉ በሙሉ ጨለማ ወረሰኝ። ሦስት ሰይጣኖች ከልቤ ውስጥ ወጡ፥ በመስኮት ሲወጡ እየሳቁ ነበር።

ሰውነቴን ስለቅ፥ ዞር አልኩኝ እናም ኢየሱስ ከኋላዬ ቆሞ ነበር። ጸጉሩ ወርቃማ ነጭ ነበር፤ ነጭ ልብስ በወርቃማ መቀነት አድርጎ ነበር። ጫማዎቹ ወርቃማ ነጠላ ጫማ ነበሩ፥እናም ሲራመድና ሲያወራ በእርጋታ ነበር። በዙሪያው ሁሉ ብርሃን ነበር እናም ነፍሴ አስቀድማ አውቃዋለች።

ወደ እርሱ ተራመድሁና ጠየቅሁት፤ “*ኢየሱስ ሆይ፥ የት ነበርክ፥ አንተን እየፈለግሁህ ነበር።*” በጣም በልስላሴ ተናገረ እንዲህ አለኝ፤ “*ፈጽሞ አልተውሁህም፥ ሁሉ ጊዜም ከጎንህ ነበርኹ። ሁል ጊዜም ንስሐ እንድትገባና የአብን ፈቃድ እንድትፈጽም እየጠበቅሁህ ነበር።*”

ታውቃላችሁ፥ ከጥቂት አመታት በፊት እንድሰብክ ተጠርቼ ነበር። እንዲ ብዬ ነበር፥ ጌታ ሆይ እሄዳለሁ፥ ነገር ግን በዛ ፈንታ ሸሸሁ።  እንዲህ አልሁኝ፥ ላደርገው አልችልም፥ በጣም ወጣት ነኝ። እግዚአብሔር ሲጣራና በህይወታችሁ ጣልቃ ሲገባ፥እሺ ከማለት ውጪ እምቢ ማለት አትችሉም።

ከዛም ለኢየሱስ፥“*ሌላ ሠላሳ ዓመት እኖራለሁ ብዬ አስቤ ነበር*” አልሁት። እርሱም “*ና፥ብዙ የምታየው ነገር አለ።*” አለኝ። እጄን ያዘኝና በሆነ መንገድ ወደታች መሄድ ጀመርን። በጣም ጨለማ ነበርና ኢየሱስ ራሱ ነበር ብርሃኑ። ወዲያውም አጋንንት በዙሪያችን ይታዩኛል። ሊይዙኝ ይሞክሩ ነበር፥ ነገር ግን እንደ ትንሽ ልጅ የጌታን እጅ ጥብቅ አድርጌ ያዝኩኝ።

የነበረኝ ብቸኛው ጠባቂ እርሱ ብቻ ነበር እናም ያናግረኝ ጀመር። እንዲህ አለ “*ታውቃለህ፥አብ ባንተ በጣም ተናደል።*” ምክንያቱ እኔ ቤተ ክርስቲያን ለማስመሰል እየሄድኩና እንደ ዮናስ እየሸሸው ስለነበር ነው። ዮናስ ሊሰብክ ተጠርቶ ነበር ነገር ግን ከእግዚአብሔር ሸሸ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ለብዙ ዓመታት ይህን አድርጌአለሁ። አሁን ድንገት አገኘኝ። በኃጢአቴ እንደሞትኩ አውቄዋለሁ፥እናም አሁን በጣም ረፍዷል።


ጉዞአችንን ቀጥለን ሳለ ጌታ ስለብዙ ነገር አናገረኝ፥እኔም ብዙ ጥየቄ ጠየቅሁት። የሆነ አካባቢ ቆምንና ጌታ “*ወደ ፊት ተመልከት*” አለኝ። በርቀት የሆነ ዓይነት ብርሃን ይታየኛል። ጌታም ጠየቀኝ “*ያ ምን ይመስልሀል?*” እኔም እንዲህ አልሁኝ “*ጌታ ሆይ፥ሲያልን ይመስላል፥ምናልባት የሲያልን እሳት።*”

ጥሩ ግምት፥እየቀረብን ስንመጣ፥የዋሻ ጠርዝ ጋር ደረስን። ዋሻው በግምት ሁለት ማይል ጥልቀት እና ወደ ሦስት ማይል አካባቢ ርዝማኔ ነበረው። ወደ ታች፥እቶን ይታየኛል፥እና ሁሉም ነገር ብርቱካናማ ቀይ ነበር። መንቀጥቀጥ ጀመርሁ፥በጣም ፈርቼ ነበር። መጨረሻዬ እዛ ታች እንደሆነ አውቄዋለሁ።

ጌታ ወደታች እንድመለከት ጠየቀኝ። ወደታች ማየት እንኳን አልቻልሁም። ማለቀስና ከጌታ ጀርባ መሮጥ ጀመርሁ። ንስሐ መግባት ጀመርሁ፥ እናም ጌታ ይቅር እንዲለኝ አለቀስሁ። አሁን እስብካለሁ ጌታ ሆይ፥ አንድ እድል ስጠኝ። እንደ ህፃን እያለቀስሁ ነበር።

የሲያል ጥልቅ እስክንደርስ ድረስ እያለቀስሁ ነበር። በቃላት ሊገለጹ የማይቻል ብዙ ነገሮችን አየሁ። ቦታው በሰው ልጆች ነፍስ የተሞላ ነበር፥እናም አጋንንት በየቦታው ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ኢሳይያስ 5፡14 “*ሲኦልም ሆድዋን አስፍታለች፥ አፍዋንም ያለ ልክ ከፍታለች፤ ከበርቴዎቻቸውና አዛውንቶቻቸው ባለጠጎቻቸውም ደስተኞቻቸውም ወደ እርስዋ ይወርዳሉ።*”



በዚያ ብዙ የሰዎች ነፍሳት በእቶኑ ውስጥ ይሰቃዩ ነበር። ለቅሶና ጩኸት በየቦታው ነበር። ምንም ተስፋ የለም፥ ለጠፉት ነፍሳት ምንም ተስፋ የለም። ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስን ስላልተቀበሉት። አንዳንዶቹ ለረዥም ጊዜ ጠብቀዋል። አንዳንዶቹ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ከዛ ከእግዚአብሔር የሸሹ ናቸው። ከእግዚአብሔር መሸሽ ወደ ሲያል ነው የሚያገባችሁ። አንዴ ከገቡ መውጣት የለም።

እባካችሁ፥እጃችሁን ወደ ጌታ አንስታችሁ ይህ በእኔ እንዲሆን አትፍቀድ እንድትሉት እፈልጋለሁ።

መንገዳችንን ስንቀጥል፥መቶ ሺዎች ጥልቅ ያህል ነበርሁ። ወደዚህ የሆነ ጥልቅ ውስጥ ስንደርስ ተንሰቅስቄ እያለቀስሁ ነበር። ከውስጡ እቶን ይወጣል። ጌታ እንዲህ አለኝ “*ሰይጣን የቆፈረላችሁ ገሀነም ይህ ነው።*” እንዲህ ሲለኝ መጮህ ጀመርሁ። አለቀስሁኝ “*ጌታ ሆይ፥ ወደዚያ መሄድ አልፈልግም።*” አለቀስሁ እናም ንስሐ ገባሁ፥ጌታንም አንድ እድል እንዲሰጠኝ እየጠየቅሁ። ዮናስ በሲያል እንብርት ውስጥ ሆኖ እንዳለቀሰው አለቀስሁ።

በሉቃስ ወንጌል በአስራ ስድስተኛው ምእራፍ፥ስለ አላዛርና ስለ ሀብታሙ ሰውዬ እናነባለን። ሀብታሙ ሰውዬ የሚፈልገው ሁሉ ነበረው።

> ሉቃ16:19 *ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር።*20 *አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥*21 *ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።*22 *ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ።*23 *በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ።*24 *እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።* 25 *አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።*26 *ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።*27 *እርሱም። እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤*28 *እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።*29 *አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው።*30 *እርሱም። አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ።*31 *ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።*

ኦ ሰዎች፥ እባካችሁ ስሙ፥ ይህ እውነት ነው፥ በምትችሉት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ። ተመልሰን ስንወጣ ገለልተኛ የሆነ ቦታ ቆመን ነበር። ጌታም "*አዳምጥ።*" አለኝ። ከዛ አንድ ሴት ስታለቅስ ሰማሁ፥ በደንብና በግልጽ ይሰማኝ ነበር፥ ስትጸልይ እንዲህ አለች "*ጌታ ሆይ፥ መልሰህ አምጣው! ሌላ እድል ስጠው። ጌታ ሆይ፥ የሚያሳድጋቸው ሁለት ልጆች አሉት። ያለኝ ሁሉ እርሱ ብቻ ነው። ከእኔ አትውሰደው!*"

ጸሎት ማንኛውንም ነገር ማንቀሳቀስ እንደሚችል ታምናላችሁ? *መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።*

እናም ሴትየዋ ጸሎቷን ቀጠለች። ጌታም ጠየቀኝ "*ይህ ምን ይመስልሀል?*" እንዲህ አልሁት "*ጌታ ሆይ፥ ባለቤቴ ናት።*" አልሁትም "*ጌታ ሆይ፥ ሰማሃት፥ የማሳድጋቸው ሁለት ወንዶች ልጆች አሉኝ። የጌታን ትከሻ መንካት ጀመርሁ፥ አሁን ልሞት አልችልም፥ ቤተሰቦቼ ይፈልጉኛል።*" ብዙ ሰበብ ማምጣት ጀመርሁ፥ ነገር ግን ምንም መልስ የለም። ማልቀስ ጀመርሁ።

ባለቤቴ ጸሎቷን ቀጠለች። ለሠዓታት የሚመስል የጥበቃ ጊዜ ነበር እናም መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር አብ እነዚህን መለሰ፥ ተናገረ ድምጹም እንደብዙ ውኃዎች ነበር። እንዲህ አለኝ "***ልጄ፥ አንድ እድል ልሰጥህ ነው፥ በባለቤትህ እምነትና ጸሎት ምክንያት እምርሀለሁ። መልሼ ስልክህ እጠቀምብሀለሁ።***"

እዛ ብዙ ቃል መግባት ጀመርሁ፥ ጌታ ሆይ እሰብካለሁ። "*ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ፥ ለሰዎች ስለዚህ ቦታ እናገራለሁ፥ ጌታ ሆይ፥ ነፍሳትን እንድታድን እረዳሀለሁ*" አልኩኝ።

ከዛም ትልቅ የቴሌቪዥን መስኮት የሚመስል ያለበት ክፍል ገባን። ያለፈውንና የሚመጣውን ሕይወቴን አሳየኝ። ሕይወቴን ከህፃንነት እስከ እወቀት ድረስ ማየት ቻልሁ። ኢየሱስ ራእይን አሳየኝ፣ ሁሉን ገለጸለኝ። ሊመጡ ያላቸውን ብዙ ነገሮች አሳየኝ። እንዲህ አለኝ "***የእውነት በመጨረሻው ዘመን (በመጨረሻዎቹ ቀናት) ነው እየኖርን ያለነው። ተመልሰህ ሂድና ለሰዎች ተናገር። በቅንነት እንዲጓዙና ንስሐ እንዲገቡ ንገራቸው። ከእኔ ጋር መቃለድ አቁመው ትእዛዛቴን እንዲጠብቁ ንገራቸው።***"

ሰዎች ራሳቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀርባ እንዴት እነደሚደብቁ አሳየኝ፥ ሥራቸውን እየሸፋፈኑ በኃጢአት ይኖራሉ። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር መስማትና ማየት ይችላል። እንዲህ አለ "***እነዚህ ሰዎች በከንፈራቸው ያመልኩኛል፥ ልባቸው ግን ከእኔ ሩቅ ነው።***" ኦ የሰውን ትእዛዝ ማስተማር እንዴት እንደሚወዱ፥ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ወደ ጎን ይተዋሉ።

እንዲህ አለ "***አትፍራ፥ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፥ የምትሰማው ሁሉ እውነት ነው።***" አለኝም "***ጆሮ ያለው ሁሉ ይስማ፥ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ይስማ።***" ሦስት ጥቅሶችን፥ ማስጠንቀቂያዎችን ሰጠኝ። የመጀመሪያው ጥቅስ በዘዳግም 6፥15 ውስጥ ነበር።


*በመካከልህ ያለው አምላክህ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነውና የአምላክህ የእግዚአብሔር ቍጣ እንዳይነድድብህ ከምድርም ፊት እንዳያጠፋህ፥*

ሁለተኛው ጥቅስ በሉቃስ 16፥13 ውስጥ ነው።

*ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፥ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።*

ራዕይ 3:3 *እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም።*

ወንድሞቼና እህቶቼ፥ ይችን ዓለም መቼ ለቀን እንደምንሄድ አናውቅም፥ ነገ ምን እንደያዘ አናውቅም፥ ስለዚህ፥ጊዜ ሳላችሁ ከእግዚአብሔር ጋር እንድትታረቁ እጸልያለሁ።





ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ገነት ወሰደኝና በእነዚህ የወርቅ በሮች መሀከል አልፈን በወርቅ ጎዳናዎች ላይ ሄድን። ታላቅ ብዛት ያላቸው የማይቆጠሩ ሰዎች ከየነገዱ ነጫጭ እጀጠባቦችን ለብሰው አየሁ እናም ከዚህ ዙፋን ፊት ቆሙ። አንዳንዶቹ የማውቃቸው ሰዎች ነበሩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰባኪያንና ነቢያት። ሁሉም ነገር ያምራል፥ ሁሉም ሰው ደስተኛ ነው፤ በፊታቸው ላይ ያለውን ፍቅር ማየት ትችላላችሁ። ታላቅ ደስታና ሰላም ይሰማኝ ጀመር።



ዙሪያውን ስቃኝ፥ ከዛ መውጣት አልፈለግሁም። ጌታ ትልቅ የግርግዳ ሠዓትን አሳየኝ። ጠቋሚዎቹ አስራ ሁለት ሠዓት ሊሉ ተቃርበዋል፥ *ሠዓት አልቋል፥ መሄጃ ሠዓት።* እንዲህ አልሁኝ “*ጌታ ሆይ፥ መሄድ አልፈልግም፥ መቅረት እፈልጋለሁ፥ ነገር ግን መውጣት ነበረብን።*”

ተመልሰን እየመጣን እያለ፥ ምድርን እንደ ትንሽ የጎልፍ ኳስ ሆና አየኋት። ሰውነቴ ተኝቶበት ወደ ነበረበት መኝታ ቤቴ አመጣኝ። ልቤ ወዳለበት ቦታ እጁን ዘረጋ። በልቤ ዙሪያ ያለው ሥጋዬ ተከፈተ። ጌታ አሮጌውን ልቤን አወጣውና ወደ እሳት ባሕር ጣለው፥ ከዛም ሌላ አንድ አዲስ ልብ ሰጠኝ፥ በዙሪያው ያለውም ሥጋዬ ተጋጠመ። እዛው ቆሜ ነበር፥ እያየሁና እየተደነቅሁ፥ ይገርማል፤ ቆዳና አጥንት እንኳን የኢየሱስን ቃል ይሰማል።

በኋላ ላይ መጽሐፍ ቅዱሴን ስመረምር እነዚህን ከትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 36 ከቁጥር 26-27 አገኘሁ፥ እንደ ህፃን አለቀስሁ ምክንያቱም ሁሉም ነገር የተጻፈ ነው፥ ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው፤

ሕዝ.36:26-27 *አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።27 መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ፥ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።*

ከዛ በኋላ ጌታ ነፍሴን ወደ ሥጋዬ መለሳት፥ ነገር ግን አዲሱ ልቤ ገና እየሠራ አልነበረም። ባለቤቴ እጄን ይዛ ስትጸልይ ትታየኝ ነበር።

ወዲያው መኝታ ቤቴ በሺሆች መላእክት ተሞላ፥ እስከዛሬ ከሰማኋቸው ሁሉ መዝሙሮች የሚያምር ምስጋናና መዝሙር ያቀርቡ ነበር። ዜማው ብቻውን የሚያስደስት ነበር። አንዱ መልአክ ተነጥሎ ወጣና ተናገረ፥ እንዲህ አለ፤ “*የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እየመጣ ነው።*” እናም ሁሉም መላእክት ማመስገንና ማወደስ ጀመሩ።

ከዛም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በእኛ ላይ መጣ፥ ከዚያም ከራስ ጸጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ ኃጢአቴን አጠበው። አልኮልና እጽ ከሰውነቴ ወጣ። ልክ እንደ ሙቅ ውኃ ዓይነት ስሜት ተሰማኝ። ራሴን ሳየው ሁሉም ጨለማ ተወግዷል። ሙሉ በሙሉ ነጭና ንጹህ ነበርሁ።

ከአፍታ በኋላ እራሱ መልአክ ወጣ አለና እንዲህ አለ፤ “*መንፈስ ቅዱስ እየመጣ ነው።*” መላእክቱ አንደገና መዘመርና ማወደስ ጀመሩ። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ መጣና ሞላን። ነፍሴ ወደ ላይና ወደ ታች እየዘለለች ነበር። በመጨረሻ መንፈስ ቅዱስን አገኘሁ። የጌታ መንፈስ ልክ እንደ ኤሌክትሪክ ትኩስ ነበር፤ ልክ እንደ እሳት በአጥንቶቼ ውስጥ ይነድዳል።

መላእክቱ እያመሰገኑና እያወደሱ ነበር ጌታ እንደዚህ ያለው "*ልጄ፥ ሂድ ለዓለም ያሳየሁህን ንገር።*" አዲሱን ልቤን በጣቱ ነካኝና መሥራት ጀመረ። ከዛም በቀስታ ዓይኔ መገለጥ ጀመረ። ሰውነቴ ቀዝቅዞ እንደነበረ ተረዳሁ፥ በግድ ነበር የምናገረው። ባለቤቴን ምን እንደተፈጠረ ጠየቅኋት። ተመለከተችኝና እንዲህ አለችኝ "ደህና ነህ?" ከዛ ማልቀስ ጀመረች።

እስካሁን በመላ ደረቴ ዙሪያ ህመም ነበር፥ ቀዶ ጥገና እንደተደረግሁ ያህል ይሰማኝ ነበር። በጣም አቅም አንሶኝና ተጠምቼ ነበር። ወዲያው ማስታወስ ጀመርሁና ምን እንደተፈጠረ አስታወስሁ። ከዛ በጉልበቴ ተንበርክኬ ለቀጣዩ ሦስት ሠዓት ያህል ፀሐይ እስክትወጣ ጸለይሁ።

ከዛ ቀን ጀምሮ ህይወቴ ተለወጠ። አመጸኛ ነበርሁ፥ ነገር ግን ጌታ በጉልበቴ አንበረከከኝ፥ እንደ ህፃን እያለቀስሁና ምህረትን እየለመንሁ። ወደ ሲዖል ነው የምሄደው፥ ዋጋ የለውም፥ ብዬ አስብ ነበር። ነገር ግን ጌታ እስኪያሳየኝ ድረስ ሲዖል ምን ያህል ስቃይ እንደሆነ አላሰብሁም ነበር። አሁን በየቀኑ ጌታን የእኔንና የቤተሰቤን ህይወት ስለመለሰው እና የወንጌል አገልጋይነትን ስለሰጠኝ አስበዋለሁ።

ወንድሞቼና እህቶቼ፥ እያስመሰላችሁ ቤተክርስቲያን እየሄዳችሁና ለሁለት ጌቶች እየተገዛችሁ እንዳይሆን እጸልያለሁ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ማሾፍ አትችሉም። በህያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ በጣም አደገኛ ነገር ነው። ስለዚህ እንዳትታለሉ፥ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። መጽሐፍ ቅዱስ፤ ሰው የዘራውን ያጭዳል፥ክፋትን የሚዘራ፥ ያንኑ ያጭዳል ይላል።

አዎ እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው፤ በርኅራኄና በምህረት የተሞላ ነው። የሁለተኛ እድሎች የሚሰጥ አምላክ ነው፥ እንዲሁም ፈራጅ አምላክም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ የሚበላ እሳት ነው ይላል። ስለዚህ መዘጋጀት ይኖርባችኋል፥ ምክንያቱም መቼ እንደምትሞቱ አታውቁምና። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ ዕብራውያን 9:27 *ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥*

ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት የምንቆምበት ጊዜ እየመጣ ነው፥ እናም መጽሐፎቻችን (የህይታችን መዝገብ) ይከፈታሉ። እዛ ነው የምትሆኑት። ይህንን ምስክርነት የሚሰማ ሁሉ እዛ ይሆናል። የማታመልጡት አንድ ቀጠሮ ነው። ይህ የመጨረሻ ጥሪያችሁ ሊሆን ይችላል፥በእግዚአብሔር ላይ አታምጹ። አስቡበት፥ ወይ ገነት ወይ ሲዖል ነው የሚሆነው። እኔ እንዳገኘሁት ዓይነት ሌላ እድል ላታገኙ ትችላላችሁ፤ ይህ (የእኔ) በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

እኔ ዛሬ በዚህ ያለሁት፥ የእኔን ምስክርነት ለእናንተ ለማጋራት ነው። እጃችሁን አንስታችሁ ለጌታ እንድትናገሩ እፈልጋለሁ፥ ስላስጠነቀቃችሁ አመስግኑት፥ ስለዚህ ውድ ሕይወት አመስግኑት። መዳን ከፈለጋችሁ ጸሎት ያስፈልጋችኋል፥በዚህች ቅጽበት ከእናንተ ጋር እንድጸልይ ፍቀዱልኝ፤

**ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ይቅር በለኝ። እንደ ግል አዳኜ አድርጌ እቀበልሀለሁ። ወደ ልቤና ወደ ህይወቴ ና። ለዘላለም ከአንተ ጋር እንድኖር ዘላለማዊ ሕይወትን ስጠኝ። የሰላምና የደስታን ሕይወት ስጠኝ። አመሰግንሀለሁ ጌታ ሆይ። በኢየሱስ ስም፥ አሜን።**

ልትጽፉልኝ ከፈለጋችሁ አድራሻዬ ይህ ነው፡

Last living days Ministries
P.O. Box 3701
ፖ.ሳ.ቁጥር 3701
Farmington, NM 87499
USA

በዚህ ምስክርነት ላይ የሰማችሁት እውነተኛ ታሪክ ነው። እኔ ናቫጆ ኢንዲያን (ወደ አሪዞናና ኒው ሜክሲኮ የፈለሱ ጎሳዎች) ነኝ። በአራቱም ማዕዘናት እኖራለሁ። ይህንን ካሴት በመላው አሜሪካ ለሚኖሩ ነባር ህዝቦች ሰጥቻለሁ። እንዲሁም ይህ ምስክርነት እንዲባዛ ፍቃዴን ሰጥቻለሁ።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ አብዲሳ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com